# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWELVE: ማጭበርበር

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ንጉሴ, ትዕግስት AND ምህረት WALK TO BUS STOP**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ንጉሴ (M, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: አቶ ሙላቱ AND ወ/ሮ ሉሊት IN A PUBLIC MINIBUS HEADING HOME**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 3: ዳንኤል HAS A CHAT WITH PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ዳንኤል (M, 15)**

**SCENE 4: አቶ ሙላቱ SHOWS UP DRUNK AT MUKARABA'S LATE AT**

**NIGHT**

- አቶ መኩሪያ (M, 55)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የአፍሪቃ ወጣቶች በሚያጋጥማቸዉ ፈተና ላይ የሚያጠነጥነዉን ተከታታይ ድራማ አስራ ሁለተኛ ክፍል ይዘን ቀርበናል። በዶይቼ ቬለ የተዘጋጀው ይህ አዲስ ትምህርታዊ ድራማየሶስት ወጣቶችን የየቀን ህይወት ይዳስሳል። ምህረት፤ ንጉሴ እና ዳንኤል የተሰኙት ወጣቶች ከተለያየ ቦታ እና ቤተሰብ በመምጣታቸዉ አስተዳደጋቸዉም እንደዛው የተለያየ ነዉ። በድራማዉ እስከ አሁን ምን እንደተከናወነ መለስ ብለን ስናይ፤ የምህረት እናት ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ስለጠፉት ሁለት መንትያ ወንድ ልጆቻቸው ማመልከት ቢፈልጉም የፖሊስ መኮንኑ ለጉዳዩ ብዙም ትኩረት አልሰጠውም :

**2. ፖሊስ (EP 11, 87):** " ልንረዳሽ አንችልም፡፡ እባክሽን የእኔ እመቤት ወደዚያ ፈቀቅ በይ፡፡ (calls out) ተረኛ!

**3. ወ/ሮ ሉሊት (LINE 91):** " እባክዎ ጌታዬ፣ ሊረዱኝ ይገባል፡፡ እስካልረዱኝ ይህንን ቦታ ለቅቄ አልሄድም።"

**4. ፖሊስ :** "አሁን ይሄን አይነት ጨዋታ የምጫወትበት ስሜት የለኝም! አስር አለቃ ይህቺን ሴት ወስደህ እስር ቤት ወርውርልኝ። "

**5. SFX PRISON CELL LOCKED**

ይህ በእንዲህ እንዳለ ምህረት ገና ዉሳኔ ላይ አልደረሰችም፡፡ ንጉሴ እና ዳንኤል፤ እንደሚፈልጓት ቢናገሯትም፤ ከሁለቱ አንዱ ብቻ ነዉ እስካሁን ልቧን ሊያማልል የቻለዉ፡

6. ምህረት (EP 09, 109): " ባየኝ ቁጥር…አየውና…ሆዴን ባርባር ይለኛል፡፡"

እና ማንን ትመርጥ ይሆን ዳንኤልን ወይስ ንጉሴን? መልካም፣ "ማጭበርበር"፣ በተሰኘው በአስራ ሁለተኛው ክፍል፣ ላይ ምን እንደሚከናወን እንይ፡፡ ንጉሴ ዳንኤልን ከምህረት ያርቅልኛል በሚል ስለ ዳንኤል ለርዕሰ መምህርት ሰብለ ተናግሯል። እናም አሁን እቅዱ እየሰራ ይመስላል፡፡ ምህረት እስከ አውቶቡስ ማቆሚያው ድረስ እንዲሸኛት ዳንኤልን እየጠበቀችው ቢሆንም ብቅ ያለው ግንዳንኤል ሳይሆን ንጉሴ ነው፡…

**SCENE 1: ንጉሴ, ትዕግስት AND ምህረት WALK TO BUS STOP**

7. SFX: SCHOOL BELL RINGS
8. SFX: PEOPLE CLOSING BOOKS AND SCRAPING CHAIRS. STUDENTS LEAVING THE CLASSROOM
9. ትዕግስት: ሃይ ምህረት፣ ፍጠኝ፡፡ እንሂድ! የሆነ ሰው በአስቸኳይ ማግኘት አለብኝ
10. ንጉሴ: ይቅርታ፣ ምህረት…እስከ አውቶቡስ ፌርማታው ድረስ ልሸኝሽ እችል አልችል እንደሆነ አላዉቅም፡፡
11. ምህረት: ውይ…ንጉሴ…አላሰብክልኝ አመሰግናለሁ፤ ግን ዳንኤል ቀድሞ እሸኝሻለሁ ብሎ ጠይቆኛል፡፡
12. ትዕግስት: (laughs) በለው! ያ ከምር ደስ ይላል ባክሽ -ምህረት ግን በኔ በኩል አዝናለሁ ፣ መሄድ አለብኝ፡፡ ባይ!

13. SFX: ትዕግስት HURRIED FOOTSTEPS

14. ምህረት: (not amused) በይ ቻዎ።

15. ንጉሴ: (surprised) እና ዳንኤል ቤት ድረስ ሊሸኝሽ ነው? ምን አልሽው?

16. ምህረት: እምልህ…እኔ እንኳ…--

17. ንጉሴ: ዳንኤል እስከ አሁን አልመጣም፣ ስለዚህ ነገሩን ትንሽ አስቢበትና እኔ ቤት ላድርስሽ? አስተማማኝ እጅ ላይ ነው ያለሽው። ተመልከች ጡንቻዎቼን ተመልከች፣ (acts out flexing his muscles)

18. ምህረት: (laughs shyly) ቀልደኛ ነህ ባክህ። ለመሆኑ አይተኸዋል? ማለቴ ዳንኤልን፣ ወደ ርዕሰ ርዕሰ መምህርቷ ቢሮ ተጠርቶ ነበር የሄደው። ከዝያ ወድያ ወደ ክፍል አልተመለሰም።

19. ንጉሴ: (pretending) አላየሁትም፣ የት እንደሆነ የማውቀው ነገር የለም። እውነቱን ለመናገር የትም ቢሆን ጉዳዬ አይደለም። ግድ የሚለኝ ስለ አንቺ፣ ስለ ምህረት ብቻ ነው።

20. ምህረት: ንጉሴ፣ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ።

21. ንጉሴ: (very excited) እሺ! ምንም ነገር ይሁን ብቻ ንገሪኝ፤ አይደለም! በጆሮዎቼ፣ በልቤ፣ በሁሉም ነገሬ እሰማሻለሁ።

22. ምህረት: ንጉሴ፣ እኔ…እኔ…እንደ ሚመስለኝ…የምወደዉ……

23. ንጉሴ: እኔም እወድሻለሁ ምህረት!

24. ምህረት፡ ይመስለኛል ዳንኤልን ነው የምወደው።

**SILENCE**

25. ምህረት፡ አዝናለሁ፣ ንጉሴ።

**26. SFX: FIST BANGING ON DESK**

27. ምህረት፡ (screams) ዉይ! አዝናለሁ!!

28. ንጉሴ፡ (furious) ምህረት፣ የምትፈልጊው ምንድን ነው? ኧህ? ገንዘብ ነው? ልሰጥሽ እችላለሁ። ምንድን ነው? ንገሪኝ!!

29. ምህረት: (indignant) ንጉሴ፣ ገንዘብ አልፈልግም። አሁን ወደ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ። እያስፈራራኸኝ ነው።

30. ንጉሴ፡ (very emotional) እና የምትፈልጊው ዳንኤልን ነው። እኔ ትተሽ ዳንኤልን መርጠሽ! ካገርሽ ልጅ ይልቅ ከላቦሪያ የመጣን ወንድ መርጠሽ?

31. ምህረት: ያ ምንም ግንኙነት የለውም!

**KW BEGIN**

32. ንጉሴ፡ (swallows hard) እሺ፤ እሺ፣ ምህረት። የራስሽ ምርጫ፣፣ የራስሽ ውሳኔ ነው። ቀረብሽ፤ ግን እማስጠነቅቅሽ ነገር ቢኖር ዳንኤል የሚሆንሽ አይመስለኝም። ማለቴ፣ ጭራሽ እኮ አታውቂውም፤ እንዳውም ከየት እንደመጣም አይገባሽም!

33. ምህረት፡ ንጉሴ፣ አንተንም እኮ አላውቅህም!!

34. ንጉሴ: እኔንማ ታውቂኛለሽ፡፡ እኔን ታውቂኛለሽ፣ ቤተሰቤን ታውቂያለሽ፡፡ አባቴ፣ አባትሽን የቤታችን ዘበኛ አድርጎ ቀጥሮታል፡፡

35. ምህረት: (shocked) አንተ የንትና……ልጅ? ልክ ነው! አቶ ጃለታ ንጉሴ ጃለታ ፡፡ ለምን እስከዛሬ እንዳልተገለፀልኝ ግን አላውቅም፡፡

36. ንጉሴ: ምህረት አባቴ ባይሆን ኖሮ ዛሬ ያለሽበት ቦታ አትደርሺም ነበር፡፡ እንደ አቶ ሙላቱ አይነት ሰካራም ሰው ማንም ከምንም እንደማይቀጥረው በደንብ ጠንቅቀሽ ታውቂያለሽ፡፡ የእኔ ቤተሰብ ግን ለአንቺ ቤተሰብ እንዲህ አልነበረም፡፡

37. ምህረት: (pissed off) ንጉሴ፣ ገደል ግባ! ከየት እና እንዴት እንደመጣሁ የምታዉቀዉ ነገር የለም፡፡ እኔ እና ቤተሰቤን ለቀቅ አድርገን፡፡

**KW END**

**38. SFX: STEPS ምህረት LEAVES**

39. ንጉሴ: ምህረት፣ ቆይ እንጂ! ይቅርታ፡፡ ስሚኝ! መናገር የፈለኩት እኮ……

**40. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: አቶ ሙላቱ AND ወ/ሮ ሉሊት IN A PUBLIC MINIBUS HEADING HOME

41. SFX: ATMO OF PEOPLE IN A PUBLIC VAN

42. አቶ ሙላቱ: (curious, in low voice) ሉሊት ለፖሊስ ምን ብለሽ ተናገርሽ? ስለ ህጻኗ ነገርሻቸው እንዴ? መቼም አታደርጊውም?

43. ወ/ሮ ሉሊት: ብሩክ እና ቅዱስ እንደጠፉ አሳውቄአለሁ፡፡ ለጊዜው የተናገርኩት እርሱ ብቻ ነው፡፡ አሁን ደስ አለህ?

44. አቶ ሙላቱ: ደስታ?! በቀረኝ ትንሽ ገንዘብ ፖሊሱን መደለል አለብኝ፡፡ ከእዛስ ይኸው መናዬን እቀልሻለሁ፡፡ እና ተደሰትሽ?

KW BEGIN

45. ወ/ሮ ሉሊት: ልጆቼን ሁሉ እንደገና ማየት ስችል ብቻ ነዉ ደስ የሚለኝ!

46. አቶ ሙላቱ: ድምጽሽን ቀነስ አድርገሽ ታደርጊው? ሰዎች የምንነጋገረውን ይሰሙናል፡፡

47. ወ/ሮ ሉሊት: (low voice) ማንም ቢሰማ ግድ የለኝም ሙላቱ ፡፡ ድምጼን እንድቀንስ አትንገረኝ፡፡ ከተጋባንበት ጊዜ ጀምሮ ስታዘዝህ ኖሬአለሁ፡፡ አሁንስ በቃኝ፤ እንዴ ናትና።፡፡

48. አቶ ሙላቱ: (angrily) ምን እያልኩ እንደሆነ እንኳ እየሰማሽኝ አይደለም? ገንዘብ አልቆብኛል ነዉ የምልሽ፡፡ እንደገና ባዶ እጅ እያጨበጨብን መሆናችንን ነው እየነገርኩሽ ያለሁት

KW END

49. **ወ/ሮ ሉሊት:** (sarcastic) ሁሌም አንተ ገንዘብ እንዳለቀብህ ነዉ። ቆይ ኧረ እንደውም ላስተካክለዉ፤ ሁሌም ገንዘብህን ጠጥተህ እንደጨረስከው ነው! ምንም አይደንቅም።

50. **አቶ ሙላቱ:** (concerned) ግን ይሄ ለየት ያለ ነው። ታውቂያለሽ አዲሱ ቤታችን ። ቆይ አሁን ኪራዩን እንዴት እንደምከፍል እና እዳዎቹን ሁሉ እንዴት እንደማወራርድ አላዉቅም? በዛ ላይ ስራዩን አቁሜያለሁ ታዲያ እንዴት እንዘልቃለን?

51. **ወ/ሮ ሉሊት:** (indifferent) እሱ የእኔ ችግር አይደለም! ከታንዲካ ጎስቋላ መንደራችን ለምን አወጣኸን? ደግሞስ ስራህን የለቀቅከው ምን ተገኝቶ ነው?

52. **አቶ ሙላቱ:** ጓደኞቼ እንዳቆም መከረውኝ ነው፤ የጓደኛ ግፊት!!

53. **ወ/ሮ ሉሊት:** (chuckles) ኧሀ? የጓደኛ ግፊት? ሙላቱ፣ ምን አይነት ጅልነት እንደሆነ ታወቃለህ? በዚህ እድሜህ በጓደኛ ግፊት ከውሳኔ የምትደርስ ከሆነ እሺ ከምህረትስ ምን እንጠብቅ?

54. **አቶ ሙላቱ:** ወደ እዚያ ጎስቋላ መንደር መመለስ ስለማልችል የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ።

55. ወ/ሮ ሉሊት: ሁሌም አንተ ችግርህ ያ ነው፣ ሙላቱ። ሁሌም ቢሆን ስለራስህ ብቻ ነዉ የምታስበዉ። ስለሌላዉስ አናንሳ፤ እንደዉ ለመሆኑ ምን አይነት አባት እና ባል ነህ አንተ?

**56.** አቶ ሙላቱ: (angry) ሉሊት፣ ከማን ጋር እየተነጋገርሽ እንደሆነ አትርሺ! አሁንም ባልሽ ነኝ። (to the driver) ሄይ! ሾፌር! እዚህ ጋር አውርደን፣

**57. SFX: VEHICLE COMES TO SUDDEN STOP**

**58. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 3: ዳንኤል HAS A CHAT WITH PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ

**59. SFX: SCHOOL ATMO**

**60. ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** ግባ፣ ዳንኤል። በሩን ዝጋው፣

**61. SFX: DOOR CLOSING**

**62. ዳንኤል:** አቤት፣ ርዕሰ መምህርት? እንድመጣ ልከውብኝ ነበር።…

**63. ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** ዳንኤል፣ ትምህርት ቤቱን እንዴት አገኘኸው?

**64. ዳንኤል:** ይህ ትምህርት ቤት? ተመችቶኛል። ቅሬታ የለኝም።

**65. ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** ጥሩ፤ በጣም ጥሩ። ከተማሪዎቼ፣ በተለይ ከውጪ አገር ከመጡ ተማሪዎቼ መስማት የሚስደስተኝ ተመችቶኛል ሲሉ ነው።

**66. ዳንኤል:** በትክል የሚሰማኝ ያ ነዉ ተስማምቶኛል።

**67. ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** ስለ ክፍል ጓደኞችህስ?

**68. ዳንኤል:** ጥሩ ናቸው፤ አብዛኞቹ ጥሩ ናቸው።

**69. ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** ጥሩ ያልሆኑት እነማን ናቸው??

**70. ዳንኤል:** (cornered) ኧ …እነርሱ ጥሩ ሳይሆኑ ቀርተው ሳይሆን ከአንዳንዶቹ ጋር እኔ ራሴ መስማማት ሳልችል ቀርቼ ነው።

71. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** **(serious tone)** ዳንኤል ካሳሁን፣ ይህ ትምህርት ቤት በስነ-ስርዓት እና በትምህርት መረሃ-ግብሩ በመላው አገሪቱ የታወቀ ነው። ስለ አንተ እ............. የሆነ ነገር ተነግሮኝ ነበር -

72. **ዳንኤል:** **(cuts her short)** ውሸት ነው፣ መምህርት፣ ውሸት ነው።

73. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** **(angry)** ዝም በል! እዚህ ትምህርት ቤት እና እዚህ ሀገር መምህር እየተናገረ ተማሪዎች አያቋርጡም። በዚህ አይነት ስለ አንተ የተነገረኝ እውነት ነው ማለት ነው። ግትር እና የማትታዘዝ ነህ! እንዲህ አይነቱን ባህሪ በቦንነ አካዳሚ ልንታገሰው አንችልም።.

74. **ዳንኤል:** **(apologetic)** ይቅርታ መምህርት! ላቋርጦት ፈልጌ አይደለም፣

75. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ :** **(strict and authoritative)** እንደ ቅጣት በየእለቱ ለአንድ ሳምንት የመማሪያ ክፍሉን ታጸዳለህ! እራሴ መጥቼ አይሀለሁ። ስለ አንተ ተጨማሪ ጥፋት ቢነገረኝ እመነኝ የማትወደዉን ነገር ትታዘዛለህ! አሁን ከዚህ ጥፋ እና ቅጣትህን ጀምር፣

76. **MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 4: አቶ ሙላቱ SHOWS UP DRUNK AT አቶ መኩሪያ' LATE AT NIGHT</u>

77. **SFX: NIGHT ATMO IN QUIET HOUSE**

78. **SFX: ELECTRIC DOORBELL RINGING**

79. አቶ መኩሪያ: (sleepy, annoyed) በዚህ ምሽት ማን ሊሆን ይችላል?

80. SFX: BABY STARTS CRYING

81. አቶ መኩሪያ: ህፃኗን ስለቀሰቀሷት አዝናለሁ ዉዴ። ለማስተኛት ሞክሪ። እኔ ማን እንደሆነ ሄጄ አያለሁ።

82. SFX: FOOTSTEPS WALKING AND FRONT DOOR BEING OPENED

83. አቶ መኩሪያ: (calls out) ማን ነው?

84. አቶ ሙላቱ: (behind gate; drunk, cheerful) ሰማ አቶ መኩሪያ! ነቃ በል! እኔ ነኝ ሙላቱ ክፈት። መነጋገር ይኖርብናል!

KW BEGIN

85. አቶ መኩሪያ: (annoyed, stays where he is) እንዴ አቶ ሙላቱ? በዚህ ውድቅት ሌሊት ምን ታደርጋለህ? አብደህ መሆን አለበት? ስንት ሰዓት እንደሆነ አውቀሀል? ቤተሰቤ በሙሉ በጊዜ ነዉ የሚተኛዉ!ተመልሰህ እንዳትመጣ የነገርኩህ መሰሎኝ ነበር!

86. አቶ ሙላቱ: (drunk) አቶ መኩሪያ። ጊዜ ገንዘብ ነው እንደሚባል ታውቃለህ። እኔ ግን እውነት መሆኑን እጠራጠራለሁ። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ቢኖረኝም ገንዘብ የለኝም! (burps)

87. አቶ መኩሪያ: (very angry) አሁን ምንድን ነዉ የምትፈልገዉ?

88. አቶ ሙላቱ: አታስገባኝም እንዴ? እንደ እዉነተኛ ወንዶች እየጠጣን መነጋገር እንችላለን?

**89. አቶ መኩሪያ፡** አቶ ሙላቱ፣ ጊዜዬን አትግደለብኝ። ምን እንደምትፈልግ ፈጥነህ ንገረኝ። ምን እንደው ልጄንን ቀሰቀስክብኝ እኮ!

**90. አቶ ሙላቱ፡** እሺ። እንንግዲያውስ ተጨማሪ ገንዘብ እፈልጋለሁ።. **(short pause)**

**KW END**

**91. አቶ መኩሪያ፡** በሩን እየከፈትኩ ነዉ,,,,,

**92. SFX: GATE DOOR OPENS AUTOMATICALLY**

**93. SFX: አቶ ሙላቱ'S DRUNKEN FOOTSTEPS APPROACHING**

**94. አቶ መኩሪያ፡** በዚህ ምሽት መጥተህ የምትጨኸብኝ እንዴት ብትደፍረኝ ነው ባክህ! **(low tone)** ተጨማሪ ገንዘብ ትፈልጋለህ? ለምን? ከፍዬህ የለም እንዴ! ምንም ዕዳ የለብኝም። ሰክረህል ወደቤትህ ሂድ!

**95. አቶ ሙላቱ፡** ሄይ! እንደዚህ አትበለኝ። ስማ አባት ለመሆን ያበቃሁህ እኔ ነኝ። ተጨማሪ ገንዘብ እፈልጋለሁ። ለማንኛውም፣ የሰጠኸኝ በቂ ስላልነበር ይመስለኛል የጨረስኩት። ገንዘቡ ለልጁ እንኳ አይበቃም።

**96. አቶ መኩሪያ (gritting his teeth)**፣ ቤሳቤስቲን ይሰጠኛል ብለህ አታስብ!

97. አቶ ሙላቱ: ጥሩ፣ አለቃዬ…ነገ ከፖሊሶች ጋር ትነጋገራለህ። ሴት ልጄን እንደሰረቅከኝ እነግራቸዋለሁ። ከነገ ጀምሮ ሴት ልጄን በህገ ወጥ መንገድ እንዲሰጥህ ጉስቁልናውን ተጠቅመህ ጫና በመፍጠር የራስህን ጥቅም የምታሳድድ ሀብታም እና በጣም የተወደደ የምክር ቤት አባል ትሆናለህ! ለሁሉም በህገ ወጥ መንገድ ልጄን አስገድደህ ለጉዲፈቻ እንደወሰድክብኝ እነግራቸዋለሁ! ከዚያም በጥቂት ሳምንታት ውሰጥ አሁንም የምክር ቤት አባልነትህመቀጠልህን እናያለን!!

98. አቶ መኩሪያ: (cautious) እሺ፣ እሺ ነገ ወደ ቢሮዬ ና። እየጠጣን በጉዳዩ ላይ እንነጋገርበታለን።

99. **TENSION-BUILDING MUSIC**

100. አቶ ሙላቱ: ምንም የምንነጋገርበት ነገር የለም ።የምፈልገው ገንዘብ ነው። ቀላል ምርጫ እኮ ነዉ፣ መኩሪያ፤ ገንዘብ ወይስ ፖሊስ?

101. **MUSIC INTERLUDE**

102. **OUTRO/ MODERATOR:**

ይኸው ዛቻ አስራ ሁለተኛዉን ክፍል ድራማ እዚህ ላይ ያጠናቅቃል። አቶ ሙላቱ አቶ መኩሪያን እያጭበረበሩት ነው- አለቅየው ይስማሙ ይሆን? በምህረት እና በዳንኤል መካከል ያለዉ ነገርስ እንዴት ይቀጥል ይሆን? ምህረት አሁን ለንጉሴ ስሜቷን በግልጽ ነግራዋለች፣ ስለሱ ምን አይነት ስሜት ይኖራት ይሆን? በቀጣይ ምን እንደሚከሰት ለማወቅ የሚቀጥለዉን ድራማ ያድምጡ። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። ድራማዉን በግል መዝገቦ ላይ መገልበጥ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!